




# በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

## መውጫ


ድርሞ /Excutive Summery/ 1

ክፍል አንድ 3

መግቢያ 3

የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር አመሰራረት 3

የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ራዕይና ተልዕኮ 5

የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት 5

የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል 6

የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ 7

የኦዲቱ አላማ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ 7

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 7

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 8

የአሰራር ስርአት መግለጫ 10

ክፍልሁለት 11

የኦዲት ግኝቶች 11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ 11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለይ እና እንዲያደራጅ ማስተባበሩንና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ 14

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒካል ሙያ እንዲሁም ስልጠና እንዲያገኙ ማስተባበሩንና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ 17

ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት ስለማስተባበሩ እና ተገቢውን ድጋፍ ስለማድረጉ በተመለከተ 23

ሚኒስቴር መስርያቤቱ አግባብ ላላቸው የክልል ተቋማት የፕሮጀክት ግምገማን አስመልክቶ ማስተባበሩን እና ተገቢውን ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ 25

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ እዲያቀርቡ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ መስራቱን በተመለከተ 31

ክፍል ሦስት 40

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion) 40

ክፍል አራት 42

የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation) ..... 42

አባሪዎች ..... i

አባሪ 1- የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር የመመዘኛ መስፈርት ..... i

/Evaluative Criteria/ ..... i

አባሪ 2-ብድር ወስደው በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በሸድ /በመስሪያ ቦታ/፣ በግብአት እጥረት እና በማሽነሪ አቅርቦት ችግር ለበርካታ ወራት ስራ ያልጀመሩ ኢንተርፕራይዞች ..... iii

አባሪ 3-በገበያ ትስስር ችግር ምክንያት ውጤታማ ያልሆኑ ኢንተርፕራይዞች / ለማሳያነት 16 ኢንተርፕራይዞች/ ..... iv

# <u>ድርሞ /Excutive Summery/</u>

**ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፣**

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር **ባለስልጣናት የሚደርሰውን የፈንዱን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም** የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች **በመገምገም** የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለማቅረቡ ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣናትና ሕዝቡ የፈንዱን አፈጻጸም በምን ደረጃ እንደሚገኝ ትክክለኛ በማስረጃ የተደገፈ መረጃ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የተፈጠሩ ችግሮች በየአመቱ ተለይተውና በሚመለከታቸው የሀገሪቷ የመንግስት ኃላፊዎች ታውቀው ከስር ከስር መፍትሔ እንዳያገኙ በማድረጉ በብድር የተሰጠው የፈንዱ ገንዘብ አመላለስ ላይ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንዲወድቅ የበኩሉን አሉታዊ ተጽእኖ እንዲኖረው ያደረገ መሆኑ፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለዩ፤ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጁ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ያልሰራ መሆኑ፡፡
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ያልሰራ መሆኑ፡፡

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርጉ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም እንዲሁም ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡
6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ **በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ** በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናትም ለፈንዱ የተመደበው 10 ቢሊዮን ብር ከ90% በላይ ወጪ ሆኖ ለወጣቶች እስከተሰራጨበት ጊዜ ድረስ የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር አላቀረቡም፡፡

# ክፍል አንድ

# መግቢያ

## የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር አመሰራረት

7. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ቀደም ሲል በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ስር የሴቶች ጉዳይ ዘርፍ እንደ አንድ ዘርፍ ተቋቅሞ የነበረ ሲሆን በወቅቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒትሩ ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ በዘርፉ የታቀዱ ተግባራት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የማቀናጀት የማስተባበርና የመከታተል ሀላፊነት ተሰጥቶት የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ቆይቷል፡፡
8. ሆኖም ባለፉት ስርዓቶች በነበረው የተዛባ የስረዓተ ጾታ ግንኙነት ሳቢያ በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን ሁለንተናዊ ችግሮች ከመፍታትና በሁሉም መስኮች ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ ተግባራቱን የሚመራ ተቋም በፌዴራል ደረጃ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
9. በዚህም መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የመስሪያ ቤቶችንና አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ ራሱን ችሎ ሊቋቋም ችሏል፡፡ ተቋሙ ከሴቶች ባሻገርም የህጻናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ስራዎችንም በተጓዳኝ ሲያከናውን እስከ ጥቅምት 2003 ዓ.ም መቆየቱ ይታወቃል፡፡
10. ከዚያም በፌዴራል የአደረጃጀት ለውጥ መደረጉን ተከትሎ በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና በወጣቶች ሚኒስቴር በተናጠል የነበረው አደረጃጀት ወደ አንድ እንዲመጣ በመወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በአዲስ መልክ ተቋቅሞ ባለፉት አምስት አመታት በመንግስትና በህዝብ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሰፊ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

11.ይሁንና ከ2008 ዓ.ም ወዲህ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሰረት የወጣቶች ዘርፍ ከሴክተሩ ወጥቶ ቀድሞ ወደ ነበረበት እንዲመለስና ከስፖርት ዘርፍ ጋር እንዲቀላቀል ሲደረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም በአዲስ መልክ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሴቶችና ሕጻናት ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

12.በአሁኑ ወቅት በ2011 ዓ/ም መንግስት በፌዴራል ደረጃ ባደረገው የመስሪያቤቶች የአደረጃጀት ለውጥ ቀድሞ በ2003 ዓ/ም ወደ ነበረው አደረጃጀት እና ስያሜ ተቀይሮ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ተብሎ እንዲጠራ ተደርጓል፡፡

13.የልማት ግቦቻችን ስኬት በሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶችን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፤ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤ ወጣቶች ያላቸውን ዕምቅ የማምረት አቅም ተጠቅመው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ለማቅረብ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

14.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የአዋጅ ቁጥር 995/2009 **ዓ/ም** ታውጇል፤፤በዚህ አዋጅ መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቅደም ተከተል ፈንዱን ለማስተግበር መመሪያና ደንቦች የማውጣት፣ በፈንዱ ዙሪያ ስልጣን ያላቸው አካላት የማስተባበርና የመደገፍ እንዲሁም ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም በአዋጁ የተሰጧቸው ተግባርና ኃላፊነቶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ስለነበሩ  የክዋኔ ኦዲቱን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሦስቱ የመንግስት መ/ቤቶች የኦዲት ስራው ተከናውኗል፡፡

15.የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የክዋኔ ኦዲት የኦዲት አካባቢው የሚሸፍነው የኦዲቱ ወሰን የ2009 እና 2010 በጀት አመት የፈንዱ አፈጻጸም ሲሆን፤  የኦዲት ስራው ማለትም የዳሰሳ፣ የቅኝት እና አብዛኛው የዝርዝር ኦዲት ስራው የተሰራው የወጣቶች ዘርፍ በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ስር በነበረበት ወቅት ነው፡፡

16.የተወሰነ የዝርዝር ኦዲት እና የኦዲት ሪፖርቱ ስራ የወጣቶች ዘርፍ የሚመለከት ተግባርና ኃላፊነት በአዲሱ የመንግስት አወቃቀር ከወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ወደ ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ከተላለፈ በኋላ ነው፡፡

17.የኦዲት ሪፖርቱ በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተናጠል የተሰራ ሲሆን፤ ቀጥሎ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት በአዲሱ የመንግስት መዋቅራዊ አደረጃጀት መሰረት የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ላይ የተሰራ ቢሆንም፤ የኦዲት ሽፋኑ እንደሚያመላክተው ከመጋቢት 2009 ዓ/ም እስከ 2010 በጀት አመት መጨረሻ በአዋጁ መሰረት ሲሰራው የነበረው የቀድሞ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር መሆኑ ታሳቢ ይደረግ፡፡

# የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ራዕይና ተልዕኮ

## ራዕይ

18.በ2017 የአገራችን ሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ በባህል መስኮች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት፣ የህፃናት መብትና ደህንነት የተከበረባት እና የስረአተ-ፆታ እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት፡፡

## ተልዕኮ

19.የሴቶችን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የህፃናትን ማህበራዊ ደህንነትን ለማስጠበቅ፣ አለማቀፋዊና አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን ተፈፃሚ ማድረግ፣ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ የሚሰሩ አካላትን ማስተባበርና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የአቅም ግንባታ ስራ መስራት፣ አፈፃፀማቸውንም በመከታተልና በመገምገም ተፈፃሚ ማድረግ፡፡

# የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

20.በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ መሰረት ለቀድሞ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ሲሆኑ በአዲሱ የመንግስት አወቃቀር የወጣቶች ዘርፍ ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የተላለፉ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀጥለው የተዘረዘሩ ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡-

- ከፈንዱ አጠቃቀም ጋር በተገናኘ አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናትን የሥራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

- አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

# የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

## ድርጅታዊ መዋቅር

21.በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር በሚኒስቴር ዴኤታ የሚመሩ ሶስት ዘርፎች ያሉት ሲሆን እነሱም የሴቶች ዘርፍ ፣ የህፃናት ዘርፍ እና የወጣቶች ዘርፍ ናቸው ፡፡ በአጠቃላይ ሚ/ር መ/ቤቱ 16 ዳይሬክቶሬቶች አሉት ፤ በሚኒስቴር ጽ/ቤት 7 ዳይሬክቶሬቶች፣ በሴቶች ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት ስር 4 ዳይሬክቶሬት፣ በህፃናት ዘርፍ ሚኒሰቴር ዴኤታ ጽ/ቤት ስር 2 ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም በወጣቶች ዘርፍ ሚኒሰቴር ዴኤታ ጽ/ቤት ስር 3 ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሲሆን የወጣቶች ማካተት ንቅናቄ እና ተሳትፎ ዳይሬክቶሬት ፣ የወጣቶች አደረጃጀቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት እና የወጣቶች ስብዕና ልማት ዳይሬክቶሬት የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት ስር ይገኛሉ ፡፡

## የሰው ኃይል

22.ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለት አጠቃላይ የሥራ መደብ 417 ሲሆን አሁን በሰው ኃይል የተሟላው 280 ወይም 67% መሆኑ ከሰው ሀብት ከተገኘ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ

23.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ብር 10 ቢሊዮን ሲሆን የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት በጀት ነው፤ ዝርዝሩ በሰንጠረዡ ተቀምጧል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

24.በሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለመገምገም ሲሆን በስራው ወቅት የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማስፈን ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

25.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

# ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

26.ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር አንድ ዋና እና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል መዋቅር፣ የሰው ኃይልና የመረጃ ልውውጥ ስርአት ያለው ስለመሆኑ መገምገም፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፈንዱ አጠቃቀም ጋር በተገናኘ በአዋጅ በተሰጡት ዝርዝር ተግባራት መሰረት አግባብ ያላቸው ባለስልጣናትን የሥራ እንቅስቃሴ በማስተባበር፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ስለማድረጉ መገምገም፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

27.የኦዲት ቡድኑ አንድ ዋና እና ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን የመረጠ ሲሆን እነዚህንም የትኩረት አቅጣጫዎች ለመገምገም የሚረዱ 6 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን (Evaluative criteria) ለይቷል፡፡ በተዘጋጁት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይም የቀድሞ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት በጽሑፍና በቃል ተጠይቀው ምላሽ አልሰጡም፤ በተላከው ደብዳቤ መሰረት በ7 ተከታታይ የስራ ቀናት ምላሽ ካልሰጡ መመዘኛ መስፈርቱ እንደተቀበሉት እንደሚወሰድ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተላከው ደብዳቤ የተገለፀ በመሆኑ በዚሁ መሰረት መ/ቤታችን የመመዘኛ መስፈርቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ወስዶታል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ **በአባሪ** 1 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

28.በአጠቃላይ ኦዲቱ የተከናወነው በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር እንዲሁም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲሆን የሸፈነው ጊዜ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ በአዋጅ ከተቋቋመበት ከመጋቢት 2009 ዓ/ም እስከ 2010 በጀት አመት ያለው የሥራ አፈጻጸም ነው፡፡ የከዋኔ ኦዲት ሪፖርቱ በያንዳንዳቸው መ/ቤቶች በተናጠል ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ ይህ ሪፖርት የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የቀድሞ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በአዋጁ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡


### የኦዲቱ ዘዴ

29.በኦዲቱ ወቅት የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስቴር ዕቅድና ዕቅድ ክንውን እና የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤዎች፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስ ቢሮዎች በአዋጅ የተሰጠውን ፈንዱን የማስተዳደር ስልጣን በውክልና ያስተላለፈባቸው ሰነዶች እና ገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን የውክልና ሰነድ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እንዲተገብሩት መመሪያ ያስተላለፈበት ሰነድ፣ በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ

መስተዳድሮች የሚገኙ የፋይናንስ ቢሮዎች፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ቢሮዎች እና የወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ብድር ወስደው ወደ ስራ የገቡ ኢንተርፕራይዞችን በአካል በመገኘት ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ የሰነድ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ፣እና በመከለስ የተሰሩ ስራዎችን በአካል ተገኝቶ በመመልከት፣ በክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮች እና ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የወጣቶች የልማትና የውጤት ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራልና የክልል መንግስታት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሀገራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ሪፖርት በፌዴራል ተቋማት በክልልና በከተማ አስተዳደር ውይይት መድረክ ላይ በተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች፤ በገንዘብ ሚኒስቴር የፈንዱን መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ሁኔታዎች በተመለከተ ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በ11/11/2010 ለኦዲቱ የቀረበ ሰነድ፣ ከብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን የሥነ ሕዝብና ስታትስቲክስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የዘጠኙ ክልሎችና የሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች ከ18-34 ዕድሜ ክልል ያሉ የወጣቶች ብዛት የሚያሳይ ሰነድ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ለዘጠኙ ክልሎችና ለሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች የተደረገው የፈንዱ የገንዘብ መጠን ክፍፍል የሚያሳይ ሰነድ፣ እንዲሁም ለሦስቱም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የቀረበላቸውን ቃለ መጠይቆችና የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ እና አግባብነት ባለው መልኩ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመከለስ /በመተንተን/ ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## የአሰራር ስርአት መግለጫ

30.የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የአሰራር ስርአት መግለጫ የተዘጋጀው በኦዲቱ ሲሆን በስዕላዊ መግለጫ ይንን ይመስላል፡፡



# <u>ክፍልሁለት</u>

## <u>የኦዲት ግኝቶች</u>

### ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ

31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 / መሰረት አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
32. የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 ባስቀመጠው ትርጓሜ መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን ማለት በማናቸውም ስያሜ ቢጠራም የወጣቶችን ጉዳይ በሚመለከት ስልጣን የተሰጠው የክልል መንግስት አካል መሆኑን ይገልጻል፡፡
33. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያቤቱ የስራ ሃላፊዎች፤ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል ፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊወች፤በናሙና ተመርጠው ከታዩ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች እና የዶክሜንት ክለሳዎች መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዳላቀረበ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34.ከዚህ በተጨማሪ በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሃረሪ ክልሎች እንዲሁም ፤አዲስ አበባ መስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር የሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ የፋይናንስ ቢሮዎች፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮዎች የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የ2009 ዓ/ም እና የ2010 ዓ/ም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዳላኩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

35.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- አዋጁ የፌዴራል ዋና ፈጻሚ የሆኑትን መ/ቤቶች ያላካተተ በመሆኑ እና ለአተገባበርም አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ በፌዴራል ደረጃ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ፣ የፌዴራል የከተማ ስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ እና የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድርን በጋራ ለመስራት የጋራ ማድረጋቸው፤ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አዳራሽ **ጥቅምት** 22/2010 **ዓ/ም** በተደረገ የአፈፃፀም ግምገማ ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፣ ከንቲባዎች ፣የሚመለከታቸው አጋር አካላት እና የፌዴራል ተቋማት በተገኙበት የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም የተገመገመ መሆኑ ገልፀዋል፤፤ የቀጣይ **የ2010 ዓ/ም** የወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰጠቱን በቀን 06/02/2010 **ዓ/ም በቁጥር መ-30-**815/19 ከስራ ፈጠራ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የተሰጡትን ሃሳቦች እና አቅጣጫዎች ለሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ለሚመለከታቸው አጋር አካላት ግብረ-መልስ በጽሁፍ መላኩን ገልጸዋል፡፡እንዲሁም በየሩብ አመት እና አመታዊ ግምገማ በማድረግ ሪፖርቱ ለሚመለከተው አካላት መላኩን ገልጸዋል፡፡

36.ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ራሱን ችሎ ለብቻው ባይሆንም ከሌሎች ስራዎች ጋር በማካተት ለተወካዮች ምክር ቤት እና ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት በተለያዩ ጊዜያት ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ነገር ግን በክልሎች የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣና የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለመላካቸው ዘርዝር አፈጻጸሙ በሚያሳይ መልኩ

ሪፖርቱ እንዳልቀረበ ለወደፊቱ ግን በየክለሎች ከሚገኙ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት በማሰባሰብ ዝርዝር የፍንዱ አፈጻጸም በሚያሳይ መልኩ ለወደፊቱ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

37. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለማቅረቡ የሚያስረዳ የ2009 የሁለተኛው አጋማሽ እና አመታዊ ሪፖርት እንዲሁም የ2010 ዓ/ም የመጀመሪያው፣ የሁለተኛው አጋማ እና አመታዊ ሪፖርቶች የሚያስረዱ የሰነድ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም በየክለሎች ከሚገኙ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመላካቸው በተረጋገጠበት ወቅት እና ከላይ እንደ ሪፖርት የተጠቀሱት በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚደረጉ ስብሰባዎች ፈንዱን በተመለከተ የሚነሱ ኃሳቦች እንጂ በአዋጁ መሰረት ደረጃውና ወቅቱ የጠበቁ ሪፖርቶች ባለመሆናቸው ሪፖርት ስለመደረጉ በሚኒስቴር መስሪያቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ የተሰጠው መልስ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለማቅረቡ ምክንያት የሚንስትሮች ምክር ቤትም ሆነ የህዝብ ተወካዮች መክር ቤት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጠንካራ እና ደካማ ጎን በመለየት ፈንዱ ውጤታማ እዲሆን የሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እንዳያስቀምጡና አፋጣኝ ውሳኔዎችን እንዳያሳልፉ ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለይ እና እንዲያደራጅ ማስተባበሩንና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1/ መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን (ማለትም የወጣቶችን ጉዳይ በሚመለከት ስልጣን የተሰጠው የክልል መንግስት አካል /በአንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 8/) ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለይ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጅ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ የክልል የፋይናንስ ቢሮ የስራ ሃላፊወች፤የክልል የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳይ ቢሮዎች የስራ ሃላፊዎች፤ የክልል የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮወች(ፅ/ቤቶች)የስራ ሃላፊዎች፣ ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች መሰረት የፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን የመለየት እና እንደ አስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲደራጅ የማድረግ ስራ በሰሩበት ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ እንዳላደረገላቸው የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡፡

41. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤታቸው ከሚመለከታቸው ከፌዴራል ተቋማት እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ የገጠር ስራ ፈጠራ እና የፌዴራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት በየሩብ ዓመቱ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እየተሰሩ የመጡ መሆኑን፤ በየደረጃው መፈታት ያለባቸውን ጉዳዮችም እንዲፈቱ እየተደረገ ሲሆን በፌዴራል ደረጃ የሚፈቱ ተብሎ ከቀረቡት ጉዳዮች የኢንተርፕራይዞች ስምና ስያሜ የሚሰጠው በፌዴራል ደረጃ በመሆኑ ይህ አሰራር ለወጣት ኢንተርፕራይዞች አስቸጋሪ ሆኖ በመቆየቱ ይህንን ለመፍታት የፌዴራል ከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት ለአብነት በደብዳቤ በቁጥር 13/18-2/09 **በቀን 20/03/2009 ዓ/ም** ለሚመለከተው ተቋም ተጽፎ መልስ እንዲሰጥ መደረጉ ገልጸዋል፡፡

42. ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለመተግበር ስራ በተጀመረበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው እስከ ታች በመውረድ የመደገፍና የማስተባበር ስራ እየሰሩ እንደነበረ

በኋላ ግን እንደመጀመሪያው የማስተባበሩና የመደገፉ ስራ ተከታታይነት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል የመስራት ክፍተት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

43. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለዩ፤ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጅ ድጋፍ የተደረገላቸው ክልሎች መ/ቤቶች፣ ምንአይነት ድጋፍ፣ በማንና መቼ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ እንዳረገ ግልጽ በሆነ ምልኩ በማስረጃ በማስደገፍ ያላቀረበ በመሆኑ፡፡ በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ የተሰጠው መልስ ከዋናው መመዘኛ መስፈርት ጋር አብሮ የማይሄድ ከመሆኑም በተጨማሪ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስተባበር ድጋፍ የሚያደርግላቸው አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት (መ/ቤቶች) በማንኛውም ስያሜ ቢጠሩ በክልል የሚገኙ የወጣቶችን ጉዳይ የሚመለከታቸው ቢሮዎች እና አካላት እንጂ የፌደራል መ/ቤቶች ባለመሆናቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታው የተሰጠው መልስ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

44. እንዲሁም በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ እንደተገለጸው ተዘዋዋሪ ፈንዱ ለማስፈጸም ወደ ስራ በተገባበት ወቅት በመጀመሪያ አካቢቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እንቅስቃሴዎች ያደርግ እንደነበረ በተለያዩ ወቅቶች በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ፈንዱን በተመለከተ ይደረጉ የነበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መኖራቸው ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤ ሆኖም በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለው እና ውጤት ሊያገኝ በሚችል መልኩ የተሰሩ ስራዎች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ከክልልና ከፌደራል የሚመለከታቸው አካላት ከተደረጉ ቃለመጠይቆችና ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

45. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን ሲለዩ፤ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ሲያደራጅ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ቀጥለው ለተዘረዘሩ ችግሮች መከሰት ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ እነሱም፡-

46.በቀን 08/01/2011 ዓ/ም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት(አብክመ) ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለኦዲተሮች በቀረበ የፅሁፍ ሰነድ መሰረት በአማራ ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ስራ አጥ ወጣቶች የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተቋማቸው በየሩብ ዓመቱ በመስክ በሚያደርገው የአካል ክትትልና ድጋፍ ከዞኖች በሚቀርበው የብድር አጠቃቀም ቅሬታ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ዳሰሳ የጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ በሪቮልቪንግ ፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ ከተለዩ ችግሮች መካከል በሁሉም የስራ መስክ ብድር አለመፈቀዱ / በዕድገት ተኮር የስራ መስክ ብቻ መሆኑ፤

47.ጥር 2010 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አፈፃፀምና በወጣቶች ተጠቃሚነት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት በአስተግባሪ ተቋማት አኳያ፡-

- ✓ ቀደም ብሎ የተበደረ የቤተሰብ አባል ካለና ያልተመለሰ ብድር ካለ አበዳሪ ተቋሙ ብድር መስጠት ያለመፈለግ ፣ ወጣቶች አይመልሱም በሚል ፍራቻ ለወጣቶች ብድር ለመስጠት ስጋት መኖሩ፣
- ✓ ለወጣቶች ስራ ለመጀመር የሚያሰችል የክህሎት ስልጠና ለመስጠት መዘግየቱና ተደራጅተው ወደ ብድር ያለመምጣታቸው ፣
- ✓ ምንም እንኳ መመሪያው ከ5-7 ወጣቶች ተደራጅተው የብድር አቅርቦት ማመቻቸት እንደሚቻል ቢፈቅድም በተግባር ግን 10 ወጣት በሚል የሚፈጠር የአደረጃጀትና የብድር አቅርቦት አሰራር ችግር መኖሩ፣ ይህ የሆነው ምንም አይነት ህጋዊ የሆነና የጸደቀ መመሪያ እና ከላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች በሌሉበት ወጣቱ ተደራጅቶ ወደ ስራ እንዳይገባ እየተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡እንዲሁም
- ✓ የስራ ፈላጊ ወጣቶች 10% ቅድመ ብድር ቁጠባ ለመቆጠብ ያለመቻላቸውና ፍላጎት ያለማሳየት፡፡ /ብድር የሚጠይቁ ወጣቶች የሚበደሩትን የገንዘብ መጠን 10% ቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ እንዳለባቸው የሚያስገድድ የጸደቀና ስራ ላይ የዋለ መመሪያ በሌለበት የመቆጠብ አቅም የሌላቸው ወጣቶች ተጠቃሚ ሳይሆኑ እንደቀሩ እና የቆጠቡት የገንዘብ መጠን አነስተኛ በመሆኑ ለስራው የሚያስፈልገውን ገንዘብ በብድር እናዳያገኙ ማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል/

- ✓ በአጠቃላይ ይህ የሆነው ምንም አይነት ህጋዊ የሆነና የጸደቀ መመሪያ እና ከላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች በሌሉበት ወጣቱ ተደራጅቶ ወደ ስራ እንዳይገባ ከፍተኛ ተግዳሮቶች የተፈጠሩ መሆናቸው በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

48.በቀን 22/01/2011 ዓ/ም የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ለኦዲተሮች በቀረበው የፅሁፍ ሰነድ መሰረት፡- በተዘዋዋሪ የወጣቶች ብድር ላይ እንደማይክሮፋይናንስ ካጋጠሙ ችግሮች መካከል በደንብ የማይተዋወቁ ወጣቶች አንድ ላይ እንዲደራጁ ማድረግ ብድር እንዲወስዱ መደረጉ፤

49.ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በቀን 22/12/2010 በተዘዋዋሪ ፈንድ ዙሪያ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ ለኦዲቱ በቀረበ የሰነድ ማስረጃ መሰረት፡-

- ✓ በአግባቡ በብድሩ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወጣቶችን ለይቶ ማደራጀት ላይ ችግር መኖሩ፤
- ✓ ቅድመ ዝግጅት ሳይደረግ ብድሩ እንዲለቀቅ በሚል ብቻ ትኩረት እንደሚደረግ እንዲሁም ሁሉም ነገር ቶሎ ቶሎ እንዲከናወን የተደረገ ሲሆን ብድር የሚወስዱ ወጣቶች በዚሁ መንፈስ በመደራጀታቸው ይህ ደግሞ ጥራት ላይ ትልቅ ችግር ያመጣ መሆኑ ታውቋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒካል ሙያ እንዲሁም ስልጠና እንዲያገኙ ማስተባበሩንና ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

50.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ መሰረት አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲገኙ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ የክልል የቴክኒክ ሙያና ኢንትርፐራይዞች ልማት ቢሮዎች (ፅ/ቤቶች) የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆችና የዶክሜንት ክለሳዎች መሰረት አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤት ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ያላስተባበረ እና ተገቢውን ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

52.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤታቸው የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ውጤታማ ለማድረግ ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፣ ለሴክተር መ/ቤቶችን እና ለወጣት አደረጃጀቶች **በአዋጅና መመሪያው** ላይ ተከታታይነት ያለው ስልጠና የሰጠ ሲሆን ክልሎች ለአጋር አካላት ስልጠና መስጠት እንዳለባቸው አቅጣጫ ማስቀመጣቸው፡፡ እንደዚሁም በክትትልና ድጋፍ የታዩ ክፍተቶችን ለከፍተኛ አመራሩ በማቅረብ ለአብነት ያህል አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመመሪያው ላይ አንዳንድ ተጨማሪ መስፈርቶች በመጨመራቸው የተቋሙ ከፍተኛ ኃላፊዎች ማለትም ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ዴኤታ እና የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ም/ዳይሬክተር በአካል ተገኝተው ውይይት በማድረግ እንዲስተካከል ማድረጋቸው ገልጸዋል፡፡

53.ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለመተግበር ስራ በተጀመረበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው እስከ ታች በመውረድ የመደገፍና የማስተባበር ስራ እየሰሩ እንደነበረ በኋላ ግን እንደመጀመሪያው የማስተባበሩና የመደገፉ ስራ ተከታታይነት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል የመስራት ክፍተት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

54.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማስፈጸሚያ ህጋዊ መመሪያ በሌለበት የወጣቶች የተዘዋዋሪ ፈንድ ውጤታማ ለማድረግ ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ መመሪያ በሌለበት ለሴክተር መ/ቤቶችን እና ለወጣት አደረጃጀቶች **በመመሪያው** ላይ ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠቱ መገለጹ፤
- በዋናነት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ባላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ ሲያደርጉ ስለ ማስተባበሩ እና ስለመደገፉ የሚያስረዳ /ማለትም ለየትኛው ክልል እና ቢሮ መቼ፣ በማንና ለስንት የፈንዱ ተጠቃሚ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ሲደረግ ወይም እንዲደረግ/ የሰነድ ማስረጃ ባለማቅረቡ፣
- በቀን 06/05/2011 ዓ/ም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ አግባብ ባላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ ሲያደርጉ በወቅቱ በክልሎች ባለው መዋቅር ማለትም በጥቃቅንና አነስተኛ

ተቋማት በኩል ይሰራል ብለው በማመናቸው የማስተባበር ሆነ የመደገፍ ስራ አለመስራታቸው የገለጹ በማሆናቸው አሁን ለነባራዊ ሁኔታ ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ፣

በአጠቃላይ ለነባራዊ ሁኔታው የተሰጠው ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

55. እንዲሁም በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ እንደተገለጸው ተዘዋዋሪ ፈንዱ ለማስፈጸም ወደ ስራ በተገባበት ወቅት በመጀመሪያ አካቢቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እንቅስቃሴዎች ያደርግ እንደነበረ በተለያዩ ወቅቶች በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ፈንዱን በተመለከተ ይደረጉ የነበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መኖራቸው ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤ ሆኖም በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለው እና ውጤት ሊያገኝ በሚችል መልኩ የተሰሩ ስራዎች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ከክልልና ከፌደራል የሚመለከታቸው አካላት ከተደረጉ ቃለመጠይቆችና ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲሰጡ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ቀጥለው ለተዘረዘሩ ችግሮች መከሰት ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ እነሱም፡-

57. ጥር 2010 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አፈፃፀምና በወጣቶች ተጠቃሚነት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት፡-

**ከአስተግባሪ ተቋማት አኳያ፡-**

- ✓ ለአመራሩ፣ ለባለሙያዎችና ስራ ፈላጊ ወጣቶች በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ መመሪያና አስተዳደር ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑና በአሰራር መመሪያው ዙሪያ በቂ ስልጠና ያለመሰጠቱ ፣

**ከስራ ፈላጊ ወጣቶች አኳያ፡-**

- ✓ ዘርፍ የማማረጥ አመለካከት መኖሩ ፣
- ✓ ወጣቶች ተደራጅቶ ከመስራት ይልቅ የተቀጣሪነት ፍላጎት መኖሩ፣
- ✓ የብድር አቅርቦት በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍል መፈለግ፣

- ✓ ሁሉንም ድጋፍ ከመንግስት ብቻ መጠበቅ ለማሳየም የገበያ ትስስር በራሳቸው ጥረት ከማፈላለግ ይልቅ ከመንግስት የሚጠብቁ መሆናቸው፣
- ✓ የብድር የጠለፋ ዋስትና ለመግባት እርስ በእርስ ያለመተማመንና በጋራ የመስራት ፍላጎት አናሳ መሆን፣

58.በአዲስ የብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር  የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ሪፖርት ታህሳስ 2010 ዓ/ም አዲስ አበባ በተገኘው ማስረጃ መሰረት፡

- ✓ ቅንጅታዊ አሰራሮች እስከ ወረዳ ድረስ በሚገባው ያለመውረዳቸው፤
- ✓ ከስልጠና የወጡና የተለያዩ ድጋፎች የሚጠይቁ ኢንተርፕራይዞችን (የመስሪያ ቦታ፣ የገበያ ትስስር እና የመሳሰሉት አቅርቦት ተጠቃሚ ማድረግ ያለመቻል)

59.በቀን 08/01/2011 ዓ/ም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት(አብክመ) ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለኦዲተሮች በቀረበ የፅሁፍ ሰነድ መሰረት፤ በተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ ከተለዩ ችግሮች መካከል ብድር ለሚወስዱ ወጣቶች የተሰጠው የክህሎት ስልጠና ለበቂ ጊዜና ሙያዉን ጠንቅቆ በሚያውቁ ባለሙያዎች አለመስጠቱ፤

60.በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ለተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል የሁሉም ትኩረት የሚሻ ስለመሆኑ ለማስገንዘብ በቀን 09/10/2010 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር አብቁተ15/8924/መ.አ-4 ለአ/ብ/ክ/መ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ እና ለአ/ብ/ክ/መ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በተጻፈው የሰነድ ደብዳቤ መሰረት ቀጥለው የተዘረዘሩ የማሳያ ችግሮች መኖራቸው ለመረዳት ተችሏል፡-

- ✓ በወጣቶች ዘንድ እየታየ ያለው ከራስ የመስረቅ አደገኛ ዝንባሌ መኖሩ፤ ወጣቶችን የስራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ብድር ማቅረብ ብቻውን በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም /አ.ብ.ቁ.ተ/፣ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት እና አልፎ አልፎም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የየተቋማቸውን ጊዜና ገንዘብ ወጪ በማድረግ ለኢንተርፕራይዞች በግዢ ሂደቱ ጭምር ድጋፍ እያደረጉ እንዳለ የሚታወቅ እንደሆነ፤ ሆኖም የኢንተርፕራይዞች አባላት ገንዘቡ ለሌላ አገልግሎት ላይ ለማዋል ግዢው በኮሚቴ እንዳይሆን በርካታ ክርክር የሚያነሱ መሆናቸው፤ በዚህ ምክንያት ብቻ ብድሩን አንፈልግም ብለው የተበተኑ በጣም ብዙ መሆናቸው፤ ይህንን ሂደት አልፈው ስራ ከጀመሩ በኋላም

የጋራ ኃብታቸውን ሰርቀው የሸጡና የተበተኑ ኢንተርፕራይዞች ጉዳይ በጣም አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ፣ የዚህ ችግር ሰለባ ከሆኑት መካከል ከዚህ በታች **ሰባት ኢንትርፕራይዞች** ለማሳያነት መቅረባቸው ከታች በሰንጠረዥ ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ የኢነርፕራይዞች የመበተን አደጋ በጣም የከፋባቸው ዞኖች ልዩ ክትትል እንደሚያስፈልጋቸው፣ የተዘዋዋሪ ብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች አባላት ቁጥር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 5 እና ከዚያ በላይ እንደነበር፣ ነገር ግን የቁጥሩ መብዛት አባላቱ በተለያዩ ምክንያቶች በጋራ ከመስራት ይልቅ እየተበተኑ የኢንትርፕራይዞች ህልውና አደጋ ላይ እየወደቀ እንደሚገኝ፡፡ ይህ ችግር በሁሉም ዞኖች እየታየ ቢሆንም ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ 19 ኢንትርፕራይዞች ሙሉ በሙሉ ብድሩን ተከፋፍለው የተበተኑ መሆናቸውን የደረሳቸው ሪፖርት እንደሚያሳይ፣ በዚሁ ዞን ምዕራብ በለሳ ወረዳም ተመሳሳይ ችግር መኖሩ መረዳታቸው ከቀረበው ሰነድ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡/

61.በቀን 22/01/2011 ዓ/ም የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ለኦዲተሮች በቀረበው የፅሁፍ ሰነድ መሰረት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ላይ እንደማይክሮ ፋይናንስ ያጋጠሙ ችግሮች ከታች ተርዝርዝረዋል፡-

**በፌዴራል በኩል**

- ✓ ክልሎች በጀታቸውን አስቀድመው እንዲነገራቸው ባለመደረጉ 10 ቢሊየን ብር ለእያንዳንዱ ክልል እንደሚደርስ አድርጎ ወጣቱ እንዲያስብ ማድረጉ ፣
- ✓ መንግስት በሚድያ ለወጣቶች የሚውል ብሎ ስላወጀው የመንግስት ስጦታ የማይመለስ ተደርጎ በወጣቱ እንዲታሰብ አድርጎታል ፣
- ✓ ካለው የሃገሪቱ ፖለቲካዊ ወቅታዊ ሁኔታ ወጣቱ እንዳያምፅ እንደ አፍ መዝጊያ የተሰጠው ገንዘብ አድርጎ እንዲያሰብ ማድረጉ ፡፡

**በክልል በኩል**

- ✓ ለወጣቶች አስተሳሰባቸው የሚቀይር ስራ በሚገባ አልተሰራም ልክ እንደ ፌዴራል በየደረጃው ያለ አመራር የመንግስት ገንዘብ ነው በሚል በግፊትና በኮታ ብድር ለወጣቶች እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ✓ አስተሳሰባቸው ሊቀይር የሚችል በቂ ስልጠና እንዲያገኙ አለማድረግ ፣

**በወጣቶች በኩል**

- ✓ ብድሩን የመንግስት ስጦታ አድርጎ ማሰብ፣
- ✓ ተደራጅቶ ብድሩ ለመውሰድ ፍቃደኛ አለመሆን ወይም ተደራጅተው ብድር ከወሰዱ በኋላ ገንዘቡን ተከፋፍለው መበታተን፣ የወሰዱት ብድር ማባከን ፣ ገንዘቡን ይዞ ቦታ መቀየር መጥፋት፣

- ✓ መሰረተ ልማት አልተሟላልንም አንከፍልም ማለት፤

**በማይክሮ ፋይናንስ በኩል**

- ✓ በአስተሳሰቡ ያልታነፀ ወጣት /በብዛት /ተደራጅተው ስለሚመጡና በየደረጃው ያሉት የመንግስት አካላት በከፍተኛ ጫናና ግፊት እንዲሰጥ ስለሚደረግ ጫና ፈርቶ ዝምብሎ ብድሩን እንዲሰጥ የማድረግ ፣ ከወጣቶችና ከመንግስት አካላት ጋር የመጋጨትና የመጨቃጨቅ፣
- ✓ ዛቻና ማስፈራርያ ስለሚደርስበት ተስፋ የመቁረጥ እና ብድር የወሰዱትን ወጣቶች በድፍረት መልሱ ለማለት መቸገር
- ✓ ለድርጅታቸው ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እና ለወጣቱም የመንግስት ገንዘብ በልቶ በነጻነት /በኮንፌደንስ/ ያለ ጠያቂ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ ሁኔታ መፈጠሩ፤ የድርጅታቸው አፈጻጸም /ፐርፎርማንስ/ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ የሚያደርግና ብድር የመስጠትና የመመለስ ባህል የሚሸረሽር ከፋይናንሻል ዲሲፕሊን ውጪ የሆነ አካሄድ እንዲተገበር የሚያደርግ ፕሮግራም እንደሆነ ነው ፡፡

62.ከደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ኩሓ ቅርንጫፍ ማይ አንበሳ ንዑስቅርንጫፍ በተዘዋዋሪ ፈንዱ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍትሔ ለመጠየቅ ለደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ዋና መ/ቤት ለኦፐሬሽን ክፍል በቀን እ.ኤ.አ 31/08/2018 በደብዳቤ ቁጥር DC/MAS/Q/1539/2018 ከተላከው በተገኘው መረጃ መሰረት፡-

- ✓ ማህበራት ከፈንዱ የወሰዱት ብድር ለመክፈል ፍቃደኛ አለመሆናቸው፣
- ✓ የማህበራቱ አባላት አንድ በአንድ ከማህበሩ እንደወጡ ወይም እንደተሰናበቱ የሚያሳይ ደብዳቤ እያመጡ መሆናቸው፣
- ✓ በክሬቸር ምርት ተደራጅተው ብድር የወሰዱ ማህበራት ውል እንዲዋዋሉ በተደጋጋሚ ጊዜ ቢጠየቁም ፍቃደኛ አለመሆናቸው፡፡

63.ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በቀን 22/12/2010 በተዘዋዋሪ ፈንድ ዙሪያ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ ለኦዲቱ በቀረበ የሰነድ ማስረጃ መሰረት፡-

- ✓ ተጠቃሚዎች ለብድሩ ብቻ ተብሎ ከሌላ አካባቢ መጥተው መደራጀትና ብድሩን ከወሰዱ በኋላ አካባቢውን ለቀው እንደሚጠፉ፤
- ✓ ብድር የሚወስዱ ወጣቶች በአግባቡ ስልጠና የማይሰጣቸው ወይም የማይወስዱ መሆኑ፤
- ✓ ብድር የሚወስዱ ወጣቶች በተዘጋጀው የገቢ መስገኛ ፕሮጀክት ላይ ጥሩ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑ እና በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል የማይችሉ መሆናቸው፤
- ✓ የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ መንግስት ለወጣቶች የሰጠ እንጂ የሚመለስ ብድር ተደርጎ ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትልቅ ችግር መኖሩ እና ወጣቶች የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ እንደ ደም ካሳ የመውሰድ የግንዛቤ ችግር መኖሩ፤
- ✓ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የተቋሙ ሰራተኞች የብድር ክትትልና ብድር የማስመለስ ስራ በሚሰሩበት ወቅት የማስፈራራት ሁኔታዎች የሚታዩ መሆኑ፤
- ✓ ብድሩን የወሰዱ ወጣቶች (ማህበራት ) ለመክፈል ፍላጎት ቢኖራቸውም ሌሎች ብድሩን ለመክፈል ፍላጎት በሌላቸው ወጣቶች ዛቻና ማስፈራሪያ የሚደርስባቸው መሆኑ፤

- ✓ ከወለድ ነፃ ብድር ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ተብሎ የተዘጋጀውን ሀሳብ በተለያየ መንገድ የተዘዋዋሪ ፈንዱም ከወለድ ነጻ የሚሰጥ ነው ብሎ ወጣቱን በዚህ አቅጣጫ እንዲረዳ መደረጉ፤
- ✓ ብድር የሚወስዱ ወጣቶች አንድን ስራ ለመስራት የእውቀትና የሙያ እጥረት መኖሩ፤ የስራ ባህል አለመኖርና የስራ ስነምግባር የማነስ ችግር በሰፊው እንደሚታይ ለማወቅ መቻሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

64.በቀን 25/01/2011 ዓ/ም በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በከተማ ዙሪያ ወረዳዎችን በወያዩበት ጊዜ ከተነሱ ጥያቄዎችና ከተሰጡ ምላሾች ሪፖርት በተገኘ መረጃ መሰረት ቀጥለው የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

- ✓ በወጣቶች ዘንድ የስራ ተነሳሽነት ፍላጎት አለመኖሩ፣
- ✓ የሚሰጠው ብድር ለስራው የሚያስፍልገውን ዕቃ ከመግዛት ይልቅ በካሽ እንዲሰጣቸው መፈለጋቸው፣
- ✓ አንዳንድ ወጣቶች ላይ በተዘዋዋሪ ፈንዱ ዙሪያ የአመለካከት ችግር መኖሩ፣
- ✓ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ ማህበራት ባለመግባባት ምክንያት እና ብሩ እንከፋፈለው በማለት የሚበተኑ መሆናቸው፣
- ✓ ብድር የወሰዱ ወጣቶች ገንዘቡ ወደአካውንታቸው ቢገባላቸውም በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ስራ ሳይገቡ በመቅረታቸው ለወለድ እዳ እየተዳረጉ መሆናቸው፣

## ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት ስለማስተባበሩ እና ተገቢውን ድጋፍ ስለማድረጉ በተመለከተ

65.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

66.ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ከሚመለከታቸው በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ የክልል የወጣቶች እና ስፖርት ጉዳይ ቢሮዎች የስራ ሃላፊዎች፤የክልል የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮዎች (ፅ/ቤቶች)የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳላስተባበረ እና ተገቢውን ድጋፍ እንላደረገ ታውቋል፡፡

67.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ ማስተባበሩንና ተገቢውን ድጋፍ ስለማድረጉ ወይም ስለአለማድረጉ በማስረጃ የተደገፈ መልስ አልሰጠም፤፤

68.ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለመተግበር ስራ በተጀመረበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው እስከ ታች በመውረድ የመደገፍና የማስተባበር ስራ እየሰሩ እንደነበረ በኋላ ግን እንደመጀመሪያው የማስተባበሩና የመደገፉ ስራ ተከታታይነት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል የመስራት ክፍተት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

69.ቢሆንም በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ እንደተገለጸው ተዘዋዋሪ ፈንዱ ለማስፈጸም ወደ ስራ በተገባበት ወቅት በመጀመሪያ አካቢቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እንቅስቃሴዎች ያደርግ እንደነበረ በተለያዩ ወቅቶች በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ፈንዱን በተመለከተ ይደረጉ የነበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መኖራቸው ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤ ሆኖም በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለው እና ውጤት ሊያገኝ በሚችል መልኩ የተሰሩ ስራዎች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ከክልልና ከፌደራል የሚመለከታቸው አካላት ከተደረጉ ቃለመጠይቆችና ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

70.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርጉ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ቀጥለው ለተዘረዘሩ ችግሮች መከሰት ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ እነሱም፡-

71.ቢዝነስ ፕላን ሳያዘጋጅ እና ሳያቀርብ ተደራጅቶ ብድር የወሰደ ኢንተርፕራይዝ እንደሌለ፤ ሆኖም ለዚህ ጉዳይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት ማንዋል በማዘጋጀት ከተማ ላይ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዳስትሪያል ኤክስቴንሺን፤ በገጠር በግብርና ኤክስቴንሽንና ባለሙያዎች ቢዝነስ ፕላን እንዲዘጋጅ መደረጉ ነገር ግን የተዘጋጁት ቢዝነስ ፕላኖች የይድረስ ይድረስ የተሰሩ፣ ከሌላ ቢዝነስ ፕላን በቀጥታ ተቀድተው /ኮፒ/ ተደርገው መቅረባቸው፤ ቢዝነስ ፕላኖቹ በደንብ ባልተጠኑበት ሁኔታ ብድሩ የተሰጠ መሆኑ በቀን 22/01/2011 ዓ/ም የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

72.በቀን 22/01/2011 ዓ/ም የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ለኦዲተሮች በቀረበው የፅሁፍ ሰነድ መሰረት በተዘዋዋሪ የወጣቶች ብድር ላይ ካጋጠሙ ችግሮች መካከል ፕሮግራሙን የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን ሳያማክርና ሳያወያይ በንግድ ባንክ ቢዝነስ ፕላኑ በተሟላ ሁኔታ ተሰርቶ አለማቅረብ /አለመደገፍ/ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

73.ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በቀን 22/12/2010 በተዘዋዋሪ ፈንድ ዙሪያ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ ለኦዲቱ በቀረበ የሰነድ ማስረጃ መሰረት ወጣቶች በገቢ ማስገኛ ፕሮጀክት ትንተና መሰረት ሳይሆን አንድ ሚሊዮን ብር መውሰድና በአምስት አመት ውስጥ መክፈል አለበት የሚል ሙያን ያላገናዘበ ድምዳሜ እንደነበር ታውቋል፡፡

## ሚኒስቴር መስርያቤቱ አግባብ ላላቸው የክልል ተቋማት የፕሮጀክት ግምገማን አስመልክቶ ማስተባበሩን እና ተገቢውን ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

74.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009ዓ.ም **በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4** መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

75.ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት የስራ ሃላፊዎች፣በክልሎች ከሚገኙ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የስራ ሃላፊዎች ጋር ባካሄዳቸው ቃለ መጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ እንዳላስተባበረ እና ተገቢውን ድጋፍ እንዳላደረገ ቀጥለው በተዘረዘሩት በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡-

76.የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማትና የከ/ም/ዋ/ማ ልማት ኤጀንሲ፣ እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፣ የኦሮሚያ ቢሄራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ ዕድል ፈጠራና የከተሞች የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የከተማ የስራ ዐድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና አጀንሲ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ እና የድሬደዋ አስተዳደር የከተማ ስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የስራ ሃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ሲመልሱ የፈንዱ ተጠቃሚ ወጣቶች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም ሲያደርጉ፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ ባስተላለፉበት ወቅት የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዳላስተባበራቸው እና ተገቢውን ድጋፍ እንዳላደረገላቸው በመግለጽ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለማስተባበሩና ስለመደገፉ የሚያስረዱ ሰነዶች ማቅረብ እንደማይችሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከመስከረም እስከ ህዳር ወር 2011 ዓ/ም በኦዲት ቡድኑ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

77.በተመሳሳይ መልኩ በቀን 22/12/2010 ዓ/ም የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ የወጣቶች ኢንተርፕራይዞች ለተቋማችን ያቀረቡት ቢዝነስ ፕላን በሚመለከታቸው ገለልተኛ ባለሙያዎች የተገመገመ አለመሆኑ፤ ነገር ግን በተቋማቸው የሚደርሰውን የብድር ያለመመለስ ስጋት ለመቀነስ ሲሉ በራሳቸው ባለሙያዎች ቢዝነስ ፕላኑ ታይቶ ብድር እንዲሰጥ መደረጉ፤
- ✓ ሆኖም ተደራጅተው ብድር ለመውሰድ የሚመጡ ወጣቶች የሚያቀርቧቸው ቢዝነስ ፕላኖች ተመሳሳይ መሆናቸው፣
- ✓ ለስራው የሚያስፈልግ በቂ ውኃ በሌለበት ብሎኬት ለማምረት የሚያስችል ቢዝነስ ፕላን ተዘጋጅቶ መቅረቡ፣

- ✓ ለስራው የሚያስፈልግ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል በሌለበት የማምረቻ ማሽኖች ለመግዛት ብድር ለመጠየቅ የተዘጋጁ ቢዝነስ ፕላኖች መቅረባቸው፣
- ✓ ለስራው የሚመጥን ዕውቀት የሌላቸው ወጣቶች/ሰራተኞች ያቀፈ ቢዝነስ ፕላን ተዘጋጅቶ ብድር የሚጠየቅ መሆኑ፣

78.የብድር አቅርቦቱ ከፍተኛው መጠን አንድ ሚሊዮን ስለተባለ ብቻ ላቀረቡት የቢዝነስ ፕላን ከሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በላይ የሚጠይቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ ብድር የጠየቁ ወጣቶች አዘጋጅተው ላቀርቡት ቢዝነስ ፕላን የሚመጥን አግባብ ካለው አካል ስልጠና አለመውሰዳቸውን ለኦዲት ቡድኑ ገልጸዋል፡

79.እንዲሁም ጉዳዩን አስመልክቶ የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ሲያስረዱ ቢዝነስ ፕላን ሳያዘጋጅ እና ሳያቀርብ ተደራጅቶ ብድር የወሰደ ኢንተርፕራይዝ የለም፤ ሆኖም ለዚህ ጉዳይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት መመሪያ በማዘጋጀት ከተማ ላይ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዳስትሪያል ኤክስቴንሺን፤ በገጠር በግብርና ኤክስቴንሽንና ባለሙያዎች ቢዝነስ ፕላን እንዲዘጋጅ መደረጉ ነገር ግን የቀረቡ ቢዝነስ ፕላኖች የይድረስ ይድረስ የተሰሩ፣ ከሌላ ቢዝነስ ፕላን በቀጥታ ተቀድተው /ኮፒ/ ተደርገው መቅረባቸው፤ ቢዝነስ ፕላኖቹ በደንብ ባልተጠኑበት ሁኔታ ብድሩ የተሰጠ መሆኑ የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

80.እንዲሁም የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መሰረት ሁሉም በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ተደራጅተው ብድር የወሰዱ ኢንተርፕራይዞች ቢዝነስ ፕላን እንዳቀረቡ ገልፀው ፤ የቀረቡት ቢዝነስ ፕላኖች የማይክሮ ፋይናንስ፣ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዝ፣ የክልሉ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ተሳትፈውበት በተዘጋጀው የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተገምግሞ ለተቋማቸው ከቀረበ በኋላ የቀረበውን ቢዝነስ ፕላን ገምግመው ብድሩን እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም በቂ የኤሌክትሪክ አቅርቦት /ኃይል/ በሌለበት፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ምቹ ሁኔታዎች ሳይኖሩ ለምሳሌ መብራት፣ ስራው የሚሰራበት ሸድ የመሳሰሉ ሳይዘጋጅ እና ለሚሰራው ስራ የማይመጥን የቢዝነስ ፕላን አቅርበው ብድር የወሰዱበት ሁኔታ መኖሩ በቀን

02/02/2011 ዓ/ም የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያውች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

81. በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገሙ፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደ አግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፉ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድም ሆነ የጋራ ዕቅድ እንደሌለው ከነሐሴ 2010 ዓ/ም እስከ ታሕሳስ 2011 ዓ/ም በናሙና ከታዩ ክልሎችና ከከተማ መስተዳድር የጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅና ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በክልል ለሚገኙ ሴክተር ተቋማት /ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች/ ተከታታይነት ባለው መልኩ የአቅም መገንባት ስራዎች ወይም ኢንተርፕራይዞችን ሊደግፉ የሚያስችል ስልጠናዎች መስጠቱን ገልጸዋል፡፡

83. ነገር ግን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለመተግበር ስራ በተጀመረበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው እስከ ታች በመውረድ የመደገፍና የማስተባበር ስራ እየሰሩ እንደነበረ በኋላ ግን እንደመጀመሪያው የማስተባበሩና የመደገፉ ስራ ተከታታይነት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል የመስራት ክፍተት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

84. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የሚገኙ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው፣ ዕውቀቱ ባላቸውና ገለልተኛ በሆኑ አካላት ጋር በመሆን ሳይገመግሙ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እንዲተላፉ ባደረጉበት ሁኔታ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል ያላቸው የክልል ሴክተር ተቋማት /የወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች/ በየትኛው ክልል ለስንት የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች በሚመለከተውና ገልልተኛ ባለሙያ እንዲገመገሙ ሲደረግ ያደረጉት ድጋፍ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ባለማቅረቡ፣
- እንዲሁም በቀን 06/05/2011 ዓ/ም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ የገቢ ማመኝጫ ፕሮጅክቶች እንዴት መገምገም እንዳለባቸው ለክልሎች የላኩት ነገር እንደሌለ ለወደፊቱ

እንደሚሰሩበት የገለጹ በመሆናቸው እና አሁን ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ከተሰጠው ምላሽ ጋር የሚቃረን ሆኖ በመገኘቱ፣

በአጠቃላይ ለነባራዊ ሁኔታው የተሰጠው ምላሽ ለኦዲቱ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

85.ሆኖም በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ እንደተገለጸው ተዘዋዋሪ ፈንዱ ለማስፈጸም ወደ ስራ በተገባበት ወቅት በመጀመሪያ አካቢቢ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እንቅስቃሴዎች ያደርግ እንደነበረ በተለያዩ ወቅቶች በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ፈንዱን በተመለከተ ይደረጉ የነበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መኖራቸው ከቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፤ ሆኖም በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለው እና ውጤት ሊያገኝ በሚችል መልኩ የተሰሩ ስራዎች አለመሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ከክልልና ከፌደራል የሚመለከታቸው አካላት ከተደረጉ ቃለመጠይቆችና ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

86.ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልል ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደ አግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ቀጥለው በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንዱ ለተዘረዘሩ ችግሮች መከሰት የራሱ የሆነ ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ እነሱም፡-

87.ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ሰ/ወሎ ዞን ጽ/ቤት በቀን 05/12/2009 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር ሰ/ወ/ዞ/አማ/5885/09 ለሰ/ወሎ ዞን ቴ/ሙ.ያ ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤት መምሪያ በተጻፈው ደብዳቤ በተገኘው ማስረጃ መሰረት፤ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰ/ወሎ ዞን ከተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ብድር ወስደው አስፈላጊውን የሸድ እና የመብራት ቆጣሪ ስላልተሟላላቸው ስራ ሳይጀምሩ ብድሩ ወለድ እየቆጠረባቸው በመሆኑ ብድሩ እንዲዘጋላቸው ብድሩ ባወጡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከነዚህም መካከል የጎላ ችግር ያለባቸው ወረዳዎች ለማሳየት ያክል፡-

- በግዳን ለ10 ኢንትርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/ እና ለአንድ ኢንትርፕራይዝ የመብራት ቆጣሪ፤

- በዳውንት ለ3 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/ እና ለ2 ኢንተርፕራይዞች የመብራት ቆጣሪ፣
- በመቂት ለ26 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/ እና ለ2 ኢንተርፕራይዞች የመብራት ቆጣሪ፣
- በዋድላ ለ12 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/፣
- በላስታ ለ6 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/፣
- በጉባላፍቶ ለ1 ኢንተርፕራይዝ ሸድ /የመስሪያ ቦታ/ አለመገንባት እና በራሳቸው ገንብተው ለሸድ ያወጡት ወጪ ይተካልን የሚልና ለ2 ኢንተርፕራይዞች የመብራት ቆጣሪ፣
- በራያ ቆቦ ለ26 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/፣
- በሀብሩ ወረዳ ለ11 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/ እና ለ1 ኢንተርፕራይዝ የመብራት ቆጣሪ፣
- በቡግና ወረዳ ለ19 ኢንተርፕራይዞች ሸድ /የመስሪያ ቦታ/፣ ያልተገነባላቸው እና ያልተሟላላቸው መሆኑ ከቀረበው ሰነድ ለመረዳት ትችሏል፡፡

88.በቀን 08/01/2011 ዓ/ም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት (አብክመ) ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለኦዲት ቡድኑ በቀረበ የፅሁፍ ሰነድ መሰረት በአማራ ክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ስራ አጥ ወጣቶች የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተቋማቸው በየሩብ ዓመቱ በመስክ በሚያደርገው የአካል ክትትልና ድጋፍ ከዞኖች በሚቀርበው የብድር አጠቃቀም ቅሬታ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ዳሰሳ የጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ በሪቮልቪንግ ፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ ከተለዩ ችግሮች መካከል የግብዓት አቅርቦት /መሬት /ሼድ/ የገበያ ትስስር ሳይፈጠር ፣ የመሰረተ ልማት ተገንብቶ /መብራት ፣ ውሃ / ሳይሟላ ፣ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች አዋጪ እንደሆኑ አስቀድሞ በግምገማ ሳይረጋገጥ ብድር እንዲወስዱ መደረጉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89.በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ለተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል የሁሉም ትኩረት የሚሻ ስለመሆኑ ለማስገንዘብ በቀን 09/10/2010 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር አብቁተ15/8924/መ.አ-4 ለአ/ብ/ክ/መ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ እና ለአ/ብ/ክ/መ ቴክኒክ ሙያና

ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በተጻፈው የሰነድ ደብዳቤ መሰረት ቀጥለው የተዘረዘሩ የማሳያ ችግሮች መኖራቸው ለመረዳት ተችሏል፡- ከነዚህም መካከል-

- ✓ ብድር ወስደው በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በሸድ /በመስሪያ ቦታ/፣ በግብአት እጥረት እና በማሽነሪ አቅርቦት ችግር ለበርካታ ወራት ስራ ያልጀመሩ ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፤
- ✓ በተለያዩ ወረዳዎች በእንስሳት መኖ ማቀነባበር፣ በዳቦ መጋገር፣ በዘይት መጭመቅ፣ በእንጨት ስራ ለመሰማራት ብድር ከተሰጣቸው በኋላ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ወደስራ ያልገቡ በርካታ ኢንተርፕራይዞች መገንዘባቸውን ቀጥሎ ለማሳያነት 13 ኢንተርፕራይዞች በሰንጠረዥ ዘርዝረው ካስቀመጡት ሰነድ ለመረዳት ተችሏል፡፡ /ሰንጠረዡ **በአባሪ 2 ተያይዟል**/

90. ጥር 2010 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አፈፃፀምና በወጣቶች ተጠቃሚነት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት ከአስተግባሪ ተቋማት አኳያ ( ኮድ፡-ከአ/አው-5 እስከ አ/አው-6) የመሰረተ ልማት (መብራት ፣ውሃ፣ መንገድ) ሳይሟላላቸው እንዲሁም ለገበያና ለስራ ምቹ የመስሪያ ቦታ ሳይዘጋጅላቸው ብድር የወሰዱ ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው ለመረዳት ተችሏል ፣

91. ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በቀን 22/12/2010 በተዘዋዋሪ ፈንድ ዙሪያ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ ለኦዲቱ በቀረበ የሰነድ ማስረጃ መሰረት የመስሪያ ቦታ ሳይዘጋጅና የገበያ ትስስር ሳይፈጠር ወጣቶቹ ብድር እንዲወስዱ የሚደረጉ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ እዲያቀርቡ የማስተባበር እና የመደገፍ ስራ መስራቱን በተመለከተ

92. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተል፣

እንዲገመግም፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርብ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የአማራ፤ የኦሮሚያ፤የአዲስ አበባ መስተዳድር፤ የድሬዳዋ መስተዳድር፤ የሃረሪ እና የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አግባብነት ካላቸው ተቋማት የስራ ሃላፊዎች ጋር በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች እና የዶክመንት ክለሳዎች መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅተው ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ እንዳላስተባበረና እና ተገቢውን ድጋፍ እንዳላደረገ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል ባለስልጣናትም ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ የግማሽ አመት እና አመታዊ ሪፖርት እንዳላቀረቡ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

94. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፤ ሚኒስቴር መ/ቤት እና አጋር አካላት በጋራ በመሆን የሩብ ዓመትና አመታዊ የስራ ፈጠራ አፈፃፀም ሪፖርት የሚመለከታቸው የክልል ስራ ፈጠራ ተቋማት ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች የክልል አበዳሪ ተቋማት ኃላፊዎች ፣የወጣቶችና ስፖርት ኃላፊዎች እና ም/ኃላፊዎች በተገኙበት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች በጋራ እየተገመገመ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት በቁጥር 1/ወ.ሴ.ማ/አ-41/22 በቀን 17/09/2010 ዓ/ም ጥሪ የተደረገላቸውን ደብዳቤ በማስረጃነት በማያያዝ ገልጸዋል፡፡

95. ሆኖም በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የፈንዱ አፈጻጸም በተመለከተ ከክልል የወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች ሪፖርት እንደሚቀርብላቸው ነገር ግን ስንት ወጣቶች የፈንዱ ተጠቃሚ እንደሆኑ ከመግለጽ ውጪ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች ዝርዝር አፈጻጸም በሚያሳይ መልኩ አለመሆኑና ሌሎች በአዋጁ መሰረት በክልል ከሚገኙ የፈንዱ ተጠቃሚ ወጣቶችን ጉዳይ ከሚመለከታቸው አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት /ከክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮዎች፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ ፋይናንስ ቢሮዎች እና ከመሳሰሉ/ ሪፖርት ተልኮላቸው እንደማያውቅ፤ ለወደፊቱ ግን ብድር

ወስደው ወደ ስራ የገቡ ኢንትርፕራይዞች በምን ሁኔታ እንደሚገኙና ውጤታማነታቸው በምን ደረጃ እንዳለ በጥናት ለመለየት በሂደት እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

96. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይህንን ይበሉ እንጂ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው በክልል እና በከተማ መስተዳድር የሚገኙ ባለስልጣናት ቢሮዎች /የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንትርፕራይዝ ቢሮዎች፣ ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች.../ የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማስተባበር እና ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ የ2009 ዓ/ም አንድ፣ የ2010 ዓ/ም ሁለት የግማሽ አመት ሪፖርቶች እና የሁለቱም አመታት ዓመታዊ ሪፖርቶች ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የላኩ ስለመሆናቸው ሪፖርቶችን በማስረጃ በማስደገፍ ባለመቅረቡ፣
- እንዲሁም በቀን 06/05/2011 ዓ/ም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከ2009 ዓ/ም የመጀመሪያ ስድት ወር ሪፖርት በስተቀር አግባብ ካላቸው በክልል እና በከተማ መስተዳድር የሚገኙ ባለስልጣናት ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ የተሰራ ስራ አለመኖሩ፤ ነገር ግን ለወደፊቱ እንደሚሰሩበት የገለጹ በመሆናቸው እና አሁን ለነባራዊ ሁኔታው ከሰጡት መልስ ጋር የሚቃረን ሆኖ በመገኘቱ፣

በአጠቃላይ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ የተሰጠው ምላሽ በኦዲቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

97. በመሆኑም በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጁ 995/2009 ዓ/ም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ ተገቢውን የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ባለመስራቱ አግባብ ያላቸው የክልል ባለስልጣናት የ2009 እና የ2010

በጀት ዓመት ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዳይልኩ አድርጓል፡፡እንዲሁም ሪፖርቶቹ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ባለመላካቸው በየክልሎቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ችግሮችን በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኙ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

98. በ2011 ዓ/ም የወጣቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመንግስታዊ ድጋፎች ያሉ ማነቆዎችና የመፍትሔ ሐሳቦች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለመወያየት መነሻ እንዲሆን መስከረም 8-2011 ዓ/ም መቐለ ከተዘጋጀ ሰነድ በተገኘ መረጃ መሰረት፡-

- ✓ በመቐለ ዞን ክትትል እና ድጋፍ የሚያደርጉ ሰዎች የተለያዩ መሆናቸው፣
- ✓ ብድር ሲሰጥ ለሚያወቋቸው በተቀላጠፈ ሁኔታ ሲሰጧቸው ለማያውቋቸው ደግሞ የማዘግየት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ በእንዳሞኾኒ ወረዳ ብድር የሚጠይቁ ወጣቶች መንግስት የሰጣቸው የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ከሌላችሁ ብድር አይሰጣችሁም የማለት ሁኔታ እንዳለ፣
- ✓ የመስሪያ እና የመሸጫ ቦታ ብድሩ ሳይሰጣቸው የተከራዩ የብድሩ ተጠቃሚ ወጣቶች ብድሩ ጸድቆላቸው ስራ እስኪ ጀምሩ ድረስ ያልሰሩበት ኪራይ መክፈላቸው፣
- ✓ በወረዳ ጋንታ ኣፈሹም መጀመሪያ ለተዘዋዋሪ ፈንዱ ከተመደበው በጀት ውጪ ከተመለሰው የብድር ገንዘብ መልሶ የማበደር ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣
- ✓ በወረዳ ጋንታ አፈሹም የሚገኙ 14 ወጣቶች በሽርክና ማህበር /ከተማ/ ካልሆነ በስተቀር በገጠር ሕ/ስራ ማህበር ዕውቅና የተሰጣቸው ብድር አንሰጥም በመባላቸው ችግር ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው፣
- ✓ ከተዘዋዋሪ ፈንዱ ጋር በተያያዘ በገጠር ሕ/ስራ ማህበር የአደረጃጀት ችግር መኖሩ፣
- ✓ በማር ማኑፋክቸሪንግ ለተሰማሩ ወጣቶች ብድሩን በማመቻቸት ሁኔታ ቀልጣፋ ምላሽ አለመስጠት፣
- ✓ በተዘዋዋሪው ብድር ፈንድ ያሉ ኮሚቴዎች ሁሉም በአንድ ጊዜ የማይገኙ በመሆናቸው ብድር በሚጠይቁ ወጣቶች ብዙ መጉላላት እየተፈጠረ መሆኑ፣

- ✓ በእንስሳት ሀብት የወጣቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቀመጠውን ፓኬጅ እና ለዘርፉ የተመደበው የብድር አቅርቦት የማይጣጣም መሆኑ፤

99. በቀን 22/01/2011 ዓ/ም የደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ለኦዲተሮች በቀረበው የፅሁፍ ሰነድ መሰረት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ላይ እንደ ማይክሮ ፋይናንስ ያጋጠሙን ችግሮች ከታች ተዘርዝረዋል፡-

**በፌዴራል በኩል**

- ✓ ፕሮግራሙን የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን ሳያማክርና ሳያወያይ በንግድ ባንክ እንደሚተገበር አድርጎ በቀላል ቢሮክራሲ ፣ ያለ ቁጠባ መታወቂያ ካርድ ብቻ በመያዝ አምስት አምስት ሁነው በመደራጀት እስከ 1 ሚልዮን ብር በቀላሉ መውሰድ እንደሚችሉ በሚድያ በመነገሩ፤
- ✓ የሚደራጁት ወጣቶች በፓርትነር ሺፕ እና በፒኤልሲ ብቻ መሆኑ ለገጠር ወጣቶች ደግሞ በህ/ስ/ማህበር የሚል የተጨመረ ቢሆንም የህ/ስ/ማህበር አዋጁ ቢያንስ 12 ስለሚል ለገጠር ወጣቶች አሰቸጋሪ መሆኑ፤

**በክልሉ በኩል**

- ✓ በቂ መስሪያና መሸጫ ቦታ አለማዘጋጀት /ወጣቶች የወሰዱት ብድር ሼድና መሰረተ ልማት ለማሟላት አውለው ተጨማሪ ብድር እንዲጠይቁ ተገደዋል፤
- ✓ መሰረተ ልማት አለማሟላት ፤
- ✓ ስንት ብድር ተሰጠ ስንት በጀት ቀረ ከማለት ውጪ ብድሩ የት ደረሰ ብሎ የሚከታተልና የሚደግፍ አካል አለመኖሩ፤

100. ከደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ኩሓ ቅርንጫፍ ማይ አንበሳ ንዑስቅርንጫፍ በተዘዋዋሪ ፈነዱ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍትሔ ለመጠየቅ ለደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ ዋና መ/ቤት ለኦፕሬሽን ክፍል በቀን እ.ኤ.አ 31/08/2018 በደብዳቤ ቁጥር DC/MAS/Q/1539/2018 ከተላከው በተገኘው መረጃ መሰረት፡-

- ✓ ሁሉም ብድር የወሰዱ ማህበራት ስራ ላይ የሉም ማለት እንደሚቻል፣ ለምሳሌ ከብድር አጠቃቀም ሪፖርት እ.ኤ.አ በ10/09/2018 ሪፖርት ከተደረገው ብድር ወስደው ስራ ላይ የሌሉ 9 ማህበራት የወሰዱት የብድር መጠን በድምሩ 3172291.56 መሆኑ፤
- ✓ በአጠቃላይ ከተዘዋዋሪ ፈንዱ የተሰጠ ብድር ከሚመለሰው የማይመለሰው የብር መጠን እየበዛ በመምጣቱ የሚመለከታቸው አካላት አንድ መፍትሔ ማድረግ እንዳለባቸው መጠየቃቸው ከቀረበው የጽሁፍ ሰነድ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

101. በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማህበር ለተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል የሁሉም ትኩረት የሚሻ ስለመሆኑ ለማስገንዘብ በቀን 09/10/2010 ዓ/ም በደብዳቤ ቁጥር አብቁተ15/8924/መ.አ-4

ለአ/ብ/ክ/መ የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ እና ለአ/ብ/ክ/መ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በተጻፈው የሰነድ ደብዳቤ መሰረት፤ ኢንተርፕራይዞች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ውጤታማ መሆን የሚችሉት ያመረቱት ምርት ተወዳዳሪ ሆኖ የሚሸጥበት አስተማማኝ ገበያ እንዲያገኝ ሲደረግ እንደሆነ፤ ይህ ገበያ ደግሞ በዘላቂነት በራሳቸው በኢንተርፕራይዞች አባላት የሚመቻች ቢሆን የተዘዋዋሪው ፈንድ አስፈጻሚ ባለ ድርሻ አካላት በተለይ የኢንዳስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የሚሰጡ አካላት የገበያ ትስስር የመፍጠር ሀላፊነት እንዳለባቸው የሚታወቅ እንደሆነ፤ ነገር ግን ይህ ባለማድረጋቸው ምክንያት የችግሩ ሰለባ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፣ ለማሳያነት 16 ኢንተርፕራይዞች በሰንጠረዥ በአባሪ አያይዘው ካቀረቡት ሰነድ ለመረዳት ተችሏል፡፡ /ዝርዝሩ **በአበሪ 3** ተያይዟል/

102. በቀን 08/01/2011 ዓ/ም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት(አብክመ) ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለኦዲተሮች በቀረበ የፅሁፍ ሰነድ መሰረት፤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ስራ አጥ ወጣቶች የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተቋማቸው በየሩብ ዓመቱ በመስክ በሚያደርገው የአካል ክትትልና ድጋፍ ከዞኖች በሚቀርበው የብድር አጠቃቀም ቅሬታ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ዳሰሳ የጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ በሪቮልቪንግ ፈንድ አጠቃቀም ዙሪያ ከተለዩ ችግሮች መካከል፡-

- ✓ በየደረጃው የሚገኘው የስራ ዕድል ፈጠራ ግብረ ሀይል ተግባሩን በዕቅዱ በተያዘው መሰረት ትኩረት በመስጠት እየገመገመ ክትትልና ድጋፍ እያደረገ አለመምራቱ ፤
- ✓ የብድር ስርዓቱ የተንዛዛ መሆኑ ፤
- ✓ የግብዓት አቅርቦት /መሬት /ሼድ/ የገበያ ትስስር አለመኖሩ ፤ የመሰረተ ልማት ተገንብቶ /መብራት ፤ ውሃ / አለመሟላት ፤
- ✓ የቅድመ ቁጠባ መጠን ከፍተኛ መሆኑ፤ /በኦዲቱ ከተሰበሰበው ማስረጃ ለመረዳት እንደተቻለ በመመሪያ ላይ ያልተቀመጠ ቅድመ ቁጠባ መጠን 10 % ስራ ላይ እንዲውል በመደረጉ የፈንዱ ተጠቃሚ ወጣቶች ለስራው የሚያስፈልግ በቢዝነስ ፕላናቸው ያስቀመጡትን የገንዘብ መጠን በብድር እንዳያገኙ ያደረገ መሆኑ/
- ✓ ከወለድ ነፃ ብድር ለሚፈልጉት ዜጎች መመሪያ አለመዘጋጀቱ፤
- ✓ በፌዴራል መንግስት የተለቀቀው በጀት ካለው የወጣት ቁጥር ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ፤
- ✓ የተመደበውን ብድር በአግባቡ ለሚገባቸው ወጣቶች አለመሰራጨቱ /በአንዳድ አካባቢዎች ለአመራር ዘመድና ሀብት ለፈጠሩ ዜጎች መሰራጨቱ / ፤

- ✓ የዋስትና ችግር መኖሩ፤ /በኦዲቱ ከተሰበሰበው ማስረጃ ለመረዳት እንደተቻለ የብድሩ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወጣቶች ዋስትና ማስያዝ አለባቸው የሚል መመሪያ ሳይኖር ያለ ህጋዊ አግባብ ስራ የዋለ መሆኑ/
- ✓ ተዘዋዋሪ ብድሩ ለሼድ ግንባታ መዋሉ፤
- ✓ በብዛት በከተማ ለሚሰጡ ስራ አጥ ወጣቶች እንጂ አብዛኛዉን የገጠር አካባቢ ያካተተ አለመሆኑ፤
- ✓ ለሚገዙ ንብረቶች አብቁተ በጊዜ እንዲቀርቡ አለማድረጉ / ለምሳሌ :- የተገዛ ክሬሸር ከሻጭ ለተጠቃሚ ገቢ አለማድረግ /
- ✓ ሀላፊነት የሚወስድ ተጠያቂና አንድ ወጥ የሆነ ተቋም አለመኖሩ፤

103. እ.ኤ.አ እስከ 29/10/2018 ድረስ ከትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከደቡባዊ ዞን፣ ደ/ምብራቅ ዞንና መቐለ፣ ምብራቃዊ ዞን፣ ከጨንፈር ዓብይ ዓዲ፣ ከማዕከላዊ ዞን፣ ከሰ/ምዕራብ ዞን እና ከምዕራባዊ ዞን የተዘዋዋሪ ብድር ከወሰዱ 1180 ወጣቶች መመለስ የነበረበት ያልተመለሰ ውዝፍ ዕዳ ብር 12305539.18 መኖሩ ከትግራይ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ከወጣቶች ማሳደግና ማብቃት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከተገኘ የሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

104. ጥር 2010 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አፈፃፀምና በወጣቶች ተጠቃሚነት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት፡-

**ከአስተግባሪ ተቋማት አኳያ**

- ✓ ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ በሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቀዉን ያህል ተቋማዊ ትኩረት ያለመስጠቱ ባለሙያው የአመራሩ ተግባር ብቻ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያዎች መኖራቸው ፤
- ✓ የአስተግባሪ አካላት በቅንጅት የመስራት ችግር በጋራ ከመስራት ይልቅ ችግሮችን በሌሎች ሴክተሮች ላይ ማፈናጠር (ማሳበብ)፤
- ✓ የመሰረተ ልማት (መብራት ፣ውሃ፣ መንገድ) ያለማሟላት እንዲሁም ለገበያና ለስራ ምቹ የመስሪያ ቦታ አለመዘጋጀቱ ፣
- ✓ ከዚህ በፊት የሰለጠኑና ህጋዊ ሰውነት ጨርሰው ወደ ስራ ያልገቡትን ኢንተርፕራይዞች ተከታትሎ መፍትሄ አለመስጠት ፣
- ✓ በተቋማት በተጨባጭ ያሉ የገበያ ትስሰሮችን በጥቃቅንና አነስተኛ ከተደራጁት ኢንተርፕራይዞች ይልቅ ለግል ባለሃብቶች የመስጠት ችግር፣

**ከመመሪያና አሰራር አኳያ**

- ✓ አደረጃጀቱና የንግድ ፍቃድ አሰጣጥ በወጣቶች መኖሪያ አካባቢ /ወረዳ ሳይሆን መስሪያ ቦታ በሚያገኙበት አካባቢ መሆኑ ወጣቶችን ለእንግልት መዳረጉና ለድጋፍና ክትትል ምቹ ያለመሆኑ፣
- ✓ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ መመሪያ አደረጃጀት አባላት ቁጥር ከ 5 እስከ 7 በሚል ብቻ አስሮ ማስቀመጡ፣ **/ህጋዊ የሆነና የጸደቀ መመሪያ በሌለበት ሁኔታ የተቀመጠው ግምገማ መነሻና መሰረት የሌለውና ትክክል አለመሆኑ በኦዲቱ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል/**
- ✓ የብድር መመለሻ የዕፎይታ ጊዜ አነስተኛ መሆኑ፣
- ✓ የወለድ አከፋፈል ሁኔታ ዓመታዊ ተቀናሽ አለመሆኑ (በቀሪ ሂሳብ ላይ)፡፡

105. በአዲስ የብድርና ቁጣባ ተቋም አ/ማህበር  የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ሪፖርት ታህሳስ 2010 ዓ/ም አዲስ አበባ በተገኘው ማስረጃ መሰረት ሰልጠነው የወጡና የተለያዩ ድጋፎች የሚጠይቁ ኢንተርፕራይዞችን  (የመስሪያና የገበያ ቦታዎች እና የመሳሰሉት አቅርቦት ተጠቃሚ ማድረግ ያለመቻል ) ለመረዳት ተችሏል፡፡

106. ከኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በቀን 22/12/2010 በተዘዋዋሪ ፈንድ ዙሪያ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች በተመለከተ ለኦዲቱ በቀረበ የሰነድ ማስረጃ መሰረት፡-

- ✓ ብድሩ ከመሰጠቱ በፊትም ከተሰጠ በኋላም በተለያዩ ሚዲያዎች (የመገናኛ ብዙሃን) ወይም የተለያዩ አካላት ብድሩን በተመለከት የተለያዩ አመለካከት መኖሩ ብድሩ ላይ ያለው ግንዛቤ ብዥታ የፈጠረ መሆኑ፤
- ✓ ተበዳሪ ወጣቶች ባላቸው መረጃ፣ ማስረጃና የሙያ መስክ ማደራጀት ሳይሆን በተለያየ መንገድ የራስ የሚሉትን ሰው ተጠቃሚ ለማድረግ የመፈለግ ችግር መኖሩ፤
- ✓ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በተመለከተ ግልፅ የሆነ ደንብና መመሪያም  ወጥቶ በሱ አለመመራት ትልቅ ችግር የፈጠረ መሆኑ፤

107. በቀን 25/01/2011 ዓ/ም በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ በከተማ ዙሪያ ወረዳዎችን ባወያዩበት ጊዜ ከተነሱ ጥያቄዎችና ከተሰጡ ምላሾች ሪፖርት በተገኘ መረጃ መሰረት ቀጥለው የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

- ✓ ወጣቶች ለኢንርፕራይዙ በቢዝነስ ፕላኑ መሰረት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ልክ 10 % ለመቆጠብ እንደማይችሉ፣
- ✓ የመስሪያ ቦታ ችግር በወጣቶች ዘንድ የሚነሳ መሆኑ፣ እንዲሁም በተለያዩ ሴክተሮች /መሬት ልማት፣ ጥቃቅንና አነስተኛ፣ወረዳና ሌሎች/ ለወጣቱ የማምረቻና መሸጫ የሚሆን መሬት ችግር ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ የማይሰሩ መሆናቸው፣
- ✓ ብድር የወሰዱ ወጣቶች ገንዘቡ ወደአካውንታቸው ቢገባላቸውም በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ስራ ሳይገቡ በመቅረታቸው ለወለድ እዳ እየተዳረጉ መሆናቸው፣

# ክፍል ሦስት

## የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion)

108. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የሚደርሰውን **የፈንዱን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም** የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አላቀረበም፡፡
109. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለዩ፤ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጁ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡
110. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡
111. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርጉ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡
112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም እንዲሁም ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡

113. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት **የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም** እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ አልሰራም፡፡ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናትም ለፈንዱ የተመደበው 10 **ቢሊዮን ብር ከ**91% በላይ ወጪ ሆኖ ለወጣቶች እስከተሰራጨበት ጊዜ ድረስ የ2009 እና የ2010 በጀት ዓመት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር አላቀረቡም፡፡

# ክፍል አራት

## የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Recommendation)

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የሚደርሰውን የፈንዱን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ተከታታይነት ባለው መልኩ ሳይቆራረጥ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ችግሮቹ በወቅቱ ተለይተው በሚመለከታቸው የመንግስት የበላይ ኃላፊዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ለማስቻል፤ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

115. የኢትዮጵያ ወጣቶች ተጠቃሚ በማድረግ በሀገሪቷ የልማት እንቅስቃሴ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ለማድረግ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለዩ፤ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጁ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

116. ከፈንዱ ብድር በመውሰድ ወደ ስራ የሚገቡ ወጣቶችን በተሰማሩበት ኢንተርፕራይዝ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግና የወሰዱት ብድር በወቅቱ በመመለስ ሌላ ዕድሉን ያላገኙ ወጣቶች የፈንዱ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ እንዲያደርጉ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

117. ከተዘዋዋሪ ፈንድ ብድር በመውሰድ በወጣቶች የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ ለማድረግ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት በፕሮጀክቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ

እንዲያደርጉ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

118. ዕውቀቱ ባላቸውና ገለልተኛ በሆኑ አካላት ያልተገመገመ የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክት ውጤታማ የመሆን እድሉ የተጣበበ በመሆኑ እና ወጣቶች የሚያቀርቧቸውን ፕሮጀክቶች ለኪሳራና ለመፍረስ ከመዳረጋቸው በፊት፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገሙ እንዲሁም ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፉ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ በተጣለበት ኃላፊነት መሰረት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሪፖርት ለማቅረብ ያስችለው ዘንድ፤ አግባብ ያላቸው የክልልና የከተማ መስተዳድር ባለስልጣናት የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተሉ፣ እንዲገመግሙ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲያቀርቡ በተቀናጀ፣ በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

120. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣቶችን ተዘዋዋሪ ፈንድ በተሳካና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስፈጸም በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይተገበር ያደረጉትን ችግሮች በመለየት አዋጁ፣ መመሪያው እና ሌሎች ማስተግበሪያ መሳሪያዎች ግልጽና በሚያሰራ ሁኔታ እንዲቀርቡለት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሊጠይቅና ተፈጻሚነታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

**በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን!**

# አባሪዎች

## አባሪ 1- የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር የመመዘኛ መስፈርት

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆነው የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ.ም ነው፡፡

| ተ/ቁ | የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚውዎች የሚያንቀሳቅሷቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 /** |
| 2. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን ፈንዱን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን እንዲለይ፣ እንደአስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲያደራጅ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1/** |
| 3. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ባለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች ቴክኒካል ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 ና አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2/** |
| 4. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን በፕሮጀክትቶች ዝግጅት ለፈንዱ ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 3/** |

| | |
|---|---|
| 5. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ እንዲያስተላልፍ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4/** |
| 6. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ያለው ባለስልጣን የፈንዱ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እንዲከታተል፣ እንዲገመግም፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲያቀርብ ሊያስተባብር እና ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**/ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 995/2009 ዓ/ም የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አግባብ ያለው ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5/** |

**አባሪ 2-ብድር ወስደው በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በሸድ /በመስሪያ ቦታ/፣ በግብአት እጥረት እና በማሽነሪ አቅርቦት ችግር ለበርካታ ወራት ስራ ያልጀመሩ ኢንትርፕራይዞች**

| ተ.ቁ | ዞን/ወረዳ | የኢንተርፕራይዙ ስም | የብድር መጠን | ብድር የወሰደበት ቀን | የተሰማራበት የስራ ዘርፍ | ስራ ያልሰራባቸው ወራት | ስራ ያልጀመረበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጎንደር ከተማ | አብይ ጌታቸውና ጓደኞቹ | 800,000 | 27/07/2017 | መኖ ማቀነባበር | 11 ወራት | በመብራት ችግር |
| 2 | ጎንደር ከተማ | ታደሰ አዳነና ጓደኞቻቸው | 900,000 | 25/07/2017 | ጠጠር ማምረት | 11 ወራት | ማሽን ለመግዛት ገንዘብ ከፍለው ባለመቅረቡ |
| 3 | ጎንደር ከተማ | አዲስ ሸዋየና ጓደኞቻቸው | 256,599 | 30/09/2017 | ከብት ማድለብ | ስራ ቢጀምሩም ውጤታማ አይደሉም | የሼድ አቅርቦት ችግርና ዝባ ማጣት |
| 4 | ጎንደር ከተማ | ኢልያስ አበበና ጓደኞቻቸው | 482,000 | 18/07/2017 | በሬ ማድለብ | ስራ ቢጀምሩም ውጤታማ አይደሉም | የሼድ አቅርቦት ችግርና ዝባ ማጣት |
| 5 | አድአርቃይ | እያያው ሞላልኝና ጓደኞቻቸው | 224,100 | 27/08/2017 | ዳቦ መጋገር | 10 ወራት | በመብራት እና በዱቄት አቅርቦት ችግር |
| 6 | አድአርቃይ | ዳንኤል ሽፈራና ጓደኞቻቸው | 220,770 | 04/09/2017 | ዳቦ መጋገር | 9 ወራት | በመብራት እና በዱቄት አቅርቦት ችግር |
| 7 | አድአርቃይ | ፈንታሁን ስዩምና ጓደኞቻቸው | 405,000 | 22/07/2017 | ዘይት መጭመቅ | 11 ወራት | በመብራት ችግር |
| 8 | አድአርቃይ | አባይ በለጠና ጓደኞቻቸው | 192,500 | 24/07/2017 | እንጨት ስራ | 11 ወራት | በመብራት ችግር |
| 9 | ጃቢጠህናን | ደምሴ ዝጋለና ጓደኞቻቸው | 900,000 | | እንጨት ስራ | | የዋንዛ እንጨት እጥረት |
| 10 | ባሕር ዳር | ሞገስ አይተነውና ጓደኞቹ | 180,000 | | ብሎኬት ማምረት | | የውሃ አገልግሎት እንዲቋረጥባቸው በመደረጉ |
| 11 | ሊቦ | ሰይድ ዮሃንስና ጓደኞቻቸው | 577,800 | | ጠጠር ማምረት | | ማሽን ለመግዛት ገንዘብ ከፍለው ባለመቅረቡ |
| 12 | ደብረታቦር | ባንቲደሩ ጌታቸውና ጓደኞቻቸው | 700,000 | | ጠጠር ማምረት | | የግብዓት ድንጋይ እጥረት |
| 13 | ጅቆ | ጌታቸው ብርቱካንና ጓደኞቻቸው | 600,000 | 09/01/2018 | ጠጠር ማምረት | 5 ወራት | የተሰጣቸውን ቦታ እንዳይሰሩበት በጽሁፍ ወረዳ ስለተከለከሉ |

## አባሪ 3-በገበያ ትስስር ችግር ምክንያት ውጤታማ ያልሆኑ ኢንተርፕራይዞች / ለማሳያነት 16 ኢንተርፕራይዞች/

2. የገበያ ችግር የኢንተርፕራይዞች ሌላው ያልተፈታ ቋጠሮ ሆኖ ቀጥሏል።

ኢንተርፕራይዞች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ውጤታማ መሆን የሚችሉት ያመረቱት ምርት ተወዳዳሪ ሆኖ የሚሸጥበት አስተማማኝ ገበያ እንዲያገኝ ሲደረግ ነው። ይህ ገበያ ደግሞ በዘላቂነት በእራሳቸው በኢንተርፕራይዙ አባላት የሚመቻች ቢሆንም እኛ ባለድርሻ አካላትም በተለይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የምንሰጥ አካላት የገበያ ትስስር የመፍጠር ሃላፊነት እንዳለብን ይታወቃል። ይህ ባለመደረጉ ምክንያት የችግሩ ሰለባ ከሆኑት ኢንተርፕራይዞች መካከል የተወሰኑት ለማሳያነት ቀጥሎ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

| ተ.ቁ | ወረዳ | የኢንተርፕራይዙ ስም | የብድር መጠን | የተሰማራበት የስራ ዘርፍ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምንጃር | ትብልጥ ጌታቸውና ጓደኞቻቸው | 338,000 | የቁም እንስሳት ንግድ | በገበያ ችግር ለኪሳራ የተዳረጉ |
| 2 | ፋግታ ለከማ | ኤልያስ ቢያድግልኝና ጓደኞቻቸው | 600,000 | ጠጠር ማምረት | ጠጠር የሚገዛ አላገኙም |
| 3 | ጓንጓ ሽኩዳድ | አቤል ሙላትና ጓደኞቻቸው | 600,000 | ጠጠር ማምረት | ጠጠር የሚገዛ አላገኙም |
| 4 | ጓንጓ ሽኩዳድ | መላኩ በላይና ጓደኞቻቸው | 270,000 | ቴሌ ሴንተር | የገበያ ችግር |
| 5 | ጓንጓ ሽኩዳድ | እያና አዝመራውና ጓደኞቻቸው | 225,000 | እንጨትና ብረታ ብረት | የገበያ ችግር |
| 6 | ጃቢ ጠህናን | የጠጓው ሶስናና ጓደኞቻቸው | 630,000 | ብሎኬት ማምረት | ብሎኬት የሚገዛ አላገኙም |
| 7 | እድአርቃይ | አበበ ጽጌረዳና ጓደኞቻቸው | 594,000 | ጠጠር ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 8 | እድአርቃይ | አገሬ መሳፍንትና ጓደኞቻቸው | 181,377 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 9 | ባሕር ዳር | ዳንኤል አስናቀና ጓደኞቹ | 180,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 10 | ባሕር ዳር | ሲሳይ ግሩምና ጓደኞቹ | 270,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 11 | ባሕር ዳር | ሽዋግዛው እንዳልካቸውና ጓደኞቹ | 450,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 12 | ባሕር ዳር | ኤርሚያስ በላይነሽና ጓደኞቹ | 180,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 13 | ባሕር ዳር | ያስቻለው ተዋበና ጓደኞቹ | 180,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 14 | ባሕር ዳር | መዓዛ ማኚና ጓደኞቹ | 180,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 15 | ባሕር ዳር | ናትናዔል ጥቅሬና ጓደኞቹ | 180,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |
| 16 | ባሕር ዳር | ምኒበል አዲስ ዘመንና ጓደኞቹ | 250,000 | ብሎኬት ማምረት | ምርታቸውን የሚገዛ አላገኙም |

3